# ከኦሮሞ ህዝብ ጋር እስካልታረቀ ድረስ የኦፒዲኦ ድርጅታዊ መረጋጋት አይታሰብም፣ የአመራር አባላቱ እጣ ፈንታም ወርደት ብቻ ነው

ከኦሮሞ ህዝብ አብራክ ተወልዶ የጠላት ጉዲፈቻ ልጅ ሆኖ የገዛ ህዝቡን በጭቆና አገዛዝ ስር ያገተው ኦፒዲኦ ከጊዜ ወደ ጊዜ በውስጡ እየተባባሰ ለሚገኘው ቀውስ ገንቢ መፍትሄ ማስገኘት አልቻለም። ኦፒዲኦ ውስጥ የሚስተዋለው የረጅም ጊዜ ችግር በአጭሩ ሲቀመጥ *"ለኦሮሞነታችን እንቁም"* እና *"ለኦሮሞነታችን አንቁም"* በሚሉ ጽንሰ ሃሳቦች ላይ የተመሰረተ ነው። በጸረ ኦሮሞነት አቋዋም የጸኑት አባላቱ ሁሌም የህወሃት ጠንካራ ትብብር ስለማይለያቸው ከሃቅ ጋር ለመታረቅ የሚፍልጉትን የድርጅቱ አባላት ድምጽ በማፈንና ብሎም ከነአካቴው በማስወገዱ ረገድ እስከ ዛሬ ድረስ የቀናቸው መሆኑ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ እስከ መጨረሻው በዚህ ስኬት ሊዘልቁ እንደማይችሉ ተሰምሮበት ሊታለፍ ይገባል።

ኦፒዲኦ የመለስ ዜናዊን ሞት ተከትሎ በውስጡ ለዘመናት ሲላወስ ቆይቶ የፈነዳውን አለመግባባት ለመፍታት በብቃት ጉድለትና በውስብስብ ችግሮች ተተብትቦ በቀውስ እንደተዋጠ ይገኛል። በድርጅቱ ውስጥ የተዛመቱትን ሁለት ተቃራኒ አመለካከቶች ለማስቀረት ሲባል አንዱን አመለካከት በሌላኛው ላይ በማንገስ የአባላቱንና የአመራሩን አቋዋም አንድ የማድረጉ ጥረት አደጋ እንዳለው ስለታወቀ ቀውሱ ተድበስብሶ ከዛሬ ደርሷል። አሁንም ችግሩ እንደተድበሰበሰ ተይዞ ከመጋቢት 14-17, 2005 በሚካሄደው የኢህአዴግ ጉባኤ ላይ ለመገኘት ደፋ ቀና እየተባለ ነው። ጉባኤውን ተከትሎ በህወሃት ቀጭን ትእዛዝ ኦፒዲኦ ውስጥ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚችል ይጠረጠራል። ይህም የሚያሳየው ድርጅቱ እንደ ድርጅት በሁለት እግሩ ቆሞ የራሱን ውስጣዊ ችግሮች በፈለገው ሰአት በራሱ ስልጣን መፍታት እንደማይችል፣ እንደ አንድ የኦሮሞ ድርጅት በኦሮሞነት ስነ ልቦና ግምገማ አካሂዶ ራሱን ማጥራት እንደማይፈቀድለትና በወያኔ ጣልቃ ገብ እጅ እየተቦካ ሁሉም ነገር የሚወሰንለት መሆኑን ነው። ይህ ከኦፒዲኦ አፈጣጠር አላማ ጋር በተያያዘ የተወሰነለት እጣ ፈንታው ቢሆንም በድርጅቱ ውስጥ በራሳቸው ነጻ አእምሮ በሚያስቡ የኦሮሞ ልጆች ዘንድ "እስከ መቼ?" የሚል ጥያቄ እያጫረ በመሄድ ላይ ይገኛል።

ኦፒዲኦን አንቀው የያዙት ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች የሚመነጩት ድርጅቱ ከኦሮሞ አብራክ ተፈጥሮ የኦሮሞን ህዝብ የልብ ትርታ በማዳመጥ ፋንታ ኦሮሞን ረግጦ እየገዛ ለሚገኘው ሃይል በተላላኪነት አጎንብሶ ከማገልገሉ ነው። ለተወለደለት ህዝብ ጋሻ ሆኖ የሚሰነዘረውን የጠላት ጦር ከመመከት ይልቅ ለጠላት ሃይል ጦርና ጋሻ ሆኖ መልሶ የገዛ ህዝቡን ከመውጋቱ የሚመነጭ ችግር ነው። ኦፒዲኦ ወላጅ አባት እናት የሆነለት የተከበረው ሰፊ የኦሮሞ ህዝብ እያለለት የህወሃት የጉዲፈቻ ልጅ ሆኖ እንዲያገለግል የታወጀበት እለት ነበር እድሉ የጠመመው። ክብራቸውን ሸጠው በታማኝነት ጠላትን የማገልገል አባዜ የተጠናወታቸው የድርጅቱ የበላይ አመራሮች በተሰጠቻቸው የስልጣን ትርፍራፊ ረክተው ለጊዜው ሆዳቸውን ሞልተው ማደር ይችሉ ይሆናል። የጉዲፈቻ አባታቸው ህወሃት ካስቀመጣቸው ወንበር አንስቶ የወረወራቸው እለት ግን መውደቂያ የላቸውም። ከአብራኩ ወጥተው በከዱት የኦሮሞ ህዝብም ሆነ ወገባቸው እስኪጎብጥ ድረስ ሲያገለግሉት በኖሩት ህወሃት ዘንድ አይንህን ላፈር የተባሉ ናቸው። ለልጆቻቸውም የሚያወርሱት መልካም ስም ሊኖራቸው አይችልም። እናም የትውልድ ተወቃሽ ሆኖ መቅረት ይከተላል።

ከአንድ ህዝብ አብራክ የሚወለድ ድርጅት የዚያ ህዝብ አፍ፣ አይንና ጆሮ ሆኖ እስካላገለገለ ድረስ ከውስጥም ሆነ ከውጭ ሰላም አያገኝም። ኦፒዲኦም ከኦሮሞ አብራክ ተወልዶ ለተወለደለት ህዝቡ በቁርጠኝነት ቆሞ እስካላገለገለ ድረስ ድርጅታዊ ክብርም ሆነ የእንቅስቃሴ ስኬት መጎናጸፉ የማይታሰብ ነው። በዚህ ሁኔታ ህዝቡን ከድቶ በጠላት

ጉዲፈቻነት በታነጸ ድርጅት ውስጥ ሁሌም ኣንድ ኣይነት ኣቋዋም ሊራመድ ኣይችልም። ከድርጅቱ ኣባላት መካከል ጠላትን እያገለገሉ ሆድ ሞልቶ በማደር የሚያምኑ እንደሚኖሩ ሁሉ ይህ ኣቋዋም የማይዋጥላቸውም መኖራቸው የማይቀር ነው። ሁለቱ ተቃራኒ ኣመለካከቶች የተፋጠጡበት ድርጅት ድርጅታዊ መረጋጋት ሊያገኝ ይቸገራል።

ይህን ችግር ማስወገድ የሚቻለው በሁለት መልኩ ነው። የመጀመሪያው የጠላትን ኣላማ ለማሳካት የተሰለፉትን ኣባላት በማዳከም ድርጅቱን በትክክል የተወለደለት ህዝብ ድርጅት ማድረግ ነው። የጉዲፈቻ ልጅነቱን በማስተው ወደ እውነተኛ እናት ኣባቱ መመለስ ነው። ሁለተኛው መፍትሄ ደግሞ ለጠላት ኣላማ መሳካት የተሰለፉት ኣባላቱ ለህዝባቸው መብት መከበር የሚቆረቆሩትን ወገኖች ኣስወግደው ድርጅቱን ሙሉ በሙሉ የጠላት ምርኩዝ ማድረግ ሲቻላቸው ነው።

የመጀመሪያው መፍትሄ የወገን/ወዳጅ መፍትሄ ነው። ይሁን እንጂ ይሄኛው መፍትሄ የወያኔ ህወሃት ወታደራዊና ቢሮክራሲያዊ የበላይነት በድርጅቱ ኣናት ላይ እንደተዘረጋ እስካለ ድረስ ገቢራዊ ለመሆን እጅግ መራራ ትግልን ይጠይቃል። ይሄኛው መፍትሄ ከተሳካ ጠላት በኦሮምያ ላይ ያለውን የበላይነት የመብቱ ባለቤት ለሆነው የኦሮሞ ህዝብ ለማስረከብ ስለሚገደድ በቀላሉ ኣይደራደርም። በቁርጠኝነት በተደራጀ ዘርፈ ብዙ ትግል መረጋገጡ ግን የጊዜ ጉዳይ እንጂ የማይቀር ነው።

በሁለተኛነት የተጠቀሰው መፍትሄ ደግሞ የጠላት መፍትሄ ነው። በርግጥ ይሄኛው መፍትሄ ኦፒዲኦ ከተወለደበት ወቅት ኣንስቶ ኣንድም ጊዜ ሳይቋዋረጥ ተግባራዊ ለማድረግ ሲደከምበት የኖረ መፍትሄ ነው። ከኦፒዲኦ ኣባላት መካከል ለህዝባቸው የሚቆረቆሩትን ወገኖች ለማስወገድ በቀጣይነት ሲሰራ የቆየ ቢሆንም ጥረቱ ሙሉ በሙሉ ሊሳካ ሳይችል ከዛሬ ደርሷል። ዛሬ ኦፒዲኦ ህወሃት በሚፈልገው ልክ እያገለገለው ኣይገኝም። ለኦሮሞነታቸው የሚቆረቆሩ ህሊናዎችን ከኦፒዲኦ ወስጥ ሙሉ በሙሉ ጠራርጎ ማስወገድም የማይቻል ጉዳይ ሆኗል። ይህን ማድረግ ከተፈለገ ምናልባት የኦፒዲኦ ኣባላትን በሙሉ ኦሮሞ ካልሆኑት ወገኖች መመልመል ሊያስፈልግ ነው። እንዲህ ለማድረግ በርግጥ ለረጅም ጊዜ ጥረት ሳይደረግ ቀርቶ ኣይደለም። ነገር ግን በዚህ ተራ ቀልድ ባለንበት ክፍለ ዘመን ሰፊውን የኦሮሞ ህዝብ ማታለል የማይመስል ጉዳይ በመሆኑ ጥረቱ ያለ ውጤት ቀርቷል። የኦፒዲኦ ኣባላትን ኦሮሞ ካልሆኑት ወገኖች እየመለመሉ በስመ ኣፋን ኦሮሞ ተናጋሪነት በኦሮሞ ህዝብ ጫንቃ ላይ ለመጫን ሲሞከር የኖረው ጥረት ይባስ ብሎ ድርጅቱንና የኦሮሞን ህዝብ ጫፍና ጫፍ ላይ በማስቀመጥ ኣራራቃቸው። ከኦፒዲኦ ውስጥ ሃቀኛ የኦሮሞ ልጆችን ማስወገድ ኣልያም ወደ ዳር መግፋት መሞከሩ የሚቀጥል ከሆነ እንዲያውም ሌላ ያልተጠበቀ ኣደጋ በስርኣቱ ህልውና ላይ የሚጋብዝ መሆኑን የህወሃት ባለስልጣናት የተረዱት ይመስላል።

ስለሆነም ይህ ስልት ዛሬም በተወሰነ መልኩ ስራ ላይ እየዋለ ቢሆንም በይበልጥ ግን በስፋት የተያዘው ዘመቻ "የኦሮሞን ህዝብ ቀልብ ከኦነግ መነጠል" የሚል በመሆኑ በውድም ሆነ በግድ በርካታ ወጣቶችን በኦፒዲኦነት መመልመል ነው። በየዩኒቨርሲቲውና ኮሌጁ ሁሉ የኦሮሞ ተወላጅ ተማሪዎችን እያስገደዱ የኦፒዲኦ ኣባልነት ቅጽ ማስሞላት የዘመኑ የፖለቲካ ፋሽን መሆኑ ይታወቃል። በግድም ሆነ በውድ በኦፒዲኦ ኣባልነት የሚመለመሉት ወጣቶች በሙሉ ደግሞ ተወደደም ተጠላም በሚፈለገው ልክ ከህዝባዊ ወገንተኝነት ተላቀው ወያኔን ከልብ ማገልገል ኣይችሉም። ምንም ያህል ስራ ለማግኘት ሲሉ ተገደውና በጥቅማ ጥቅሞች ተደልለው የኦፒዲኦን ኣባልነት ቢቀበሉም ውሎ ኣድሮ የኦሮሞነታቸው ደም ተቆጥቶ ለግንቢ ለውጥ እንደሚያነሳሳቸው የማይቀር ነው። የህወሃት ኣመራር ከላያቸው ሆኖ የሚያግታቸውን ኣስተሳሰብ ሁሌም በዝምታ መዋጥ ኣይችሉም። ስለሆነም ለህዝባቸው የሚቆረቆሩና የኦሮሞን

ህዝብ ጥቅም አሳልፎ ለመስጠት ባሰፈሰፉበት ወይም ራሳችን እንሁን እና ራሳችን አንሁን የሚሉ ወገኖች ጎራ ለይተው በተፋጠጡበት ድርጅት ውስጥ ድርጅታዊ መረጋጋት ሊኖር አይችልም። ኦፒዲኦን እየናጠው የሚገኘውም ይሄው ሃቅ ነው።

ህወሃት የበላይነቱን ጠብቆ አገሪቷን መግዛት እስከቀጠለ ድረስ ኦፒዲኦ ውስጥ የሚታየው ቀውስ እልባት ማግኘት አይችልም። ወያኔዎቹ እንደ ልማዳቸው ዛሬም በኦፒዲኦ ውስጥ ቁልፍ በሚባሉ ቦታዎች ላይ ታማኝ ጀሌዎቻቸውን ለመሾም ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ ናቸው። ይህ የሹም ሽረት እርምጃ ደግሞ በየዋህነት ድርጅቱን የሚያገለግሉ በርካታ የኦሮሞ ተወላጆችን ሊመታ እንደሚችል አይካድም። ለረጅም ጊዜ ከታየው የወያኔ ህወሃት ተመክሮ መረዳት እንደሚቻለው "የጠገበ ጅብን በተራብ ጅብ መተካት" የሚል ፖሊሲ ገቢራዊ ሲሆን ቆይቷል። በዚህ ፖሊሲ መሰረት ከወገብ ጎብጠው በታማኝነት ህወሃትን ሲያገለግሉ የኖሩ የኦፒዲኦ አመራሮችን ከወንበር እያነሱ ከስር የሚመጡትን የተራቡ ግልገል ካድሬዎችን ወንበሩ ላይ በማስቀመጥ "ጠግበው የበላይ አለቆቻቸውን መዳፈር የከጀሉ" የተባሉትን አመራር አባላት ማስወገድ ነው። ግልገሉ ካድሬም በተራው ሆዱን ሞልቶ ጠግቦ መዳፈር ሲጀምር ከእግሩ ስር ወደ ላይ ለመምጣት የሚንጠራራውን ግልገል እየመዘዙ አናቱ ላይ መሾምና አሮጌውን ካድሬ አሽቀንጥሮ መወርወር ነው። ይህ ስልት ሁለት ፋይዳዎች እንዳሉት ታምኖበታል። የመጀመሪያውና ትልቁ ፋይዳ ድርጅቱ ዘላለም ከበላይ ጌቶች ጠንካራ ቁጥጥር እንዳይወጣ ይከላከላል። በድርጅቱ ውስጥ አብዮት ሊያስነሱ የሚችሉትን የእድል ቀዳዳዎችን በሙሉ ይደፍናል ተብሎ ይታሰባል። ሁለተኛው ፋይዳ ደግሞ በፕሮፓጋንዳ ፍጆታነት የሚያገለግል መሆኑ ነው። "በስልጣን ባልገው የበደሏችሁን ዋልጌ ግለሰቦች ከሃላፊነት አነሳን" እየተባለ ለህዝብ ይለፈፋል።

ስለዚህ በኑሮ ሁኔታ ተገደው አልያም በጊዜያዊ ጥቅሞች ተታለው ኦፒዲኦ ውስጥ የተሰለፉ የኦሮሞ ልጆች ከዚህ የወያኔ መንግስት አካሄድ ምን መማር ይጠበቅባቸዋል? የዚህ ጥያቄ መልስ ግልጽ ነው። እንዳለፉት ባለስልጣናት ሁሉ ልክ እንደ ሸንኮራ አገዳ እኛኪ ተመጠው ከመወርወር፣ በዚህም ስማቸውንና ታሪካቸውን አጥተው ከመዋረድ ይልቅ ቢያንስም ቢበዛም ዛሬ እጃቸው አለች በምትባለው ስልጣን ልክ እንኳዋን ታሪክ ሰርተው ማለፉ ይበጃቸዋል። ጠላት በአካፋ ዝቆ እየዘረፈ በማንኪያ ቆንጥሮ የሚደልላቸውን የገዛ ህዝባቸውና ሃገራቸው ሃብት እያዩ ራስን መሸጥ ውርደት ነው። የራስን ሃብት ሙሉ በሙሉ ከጠላት እጅ ፈልቅቆ በማውጣት ዝናን ተጎናጽፎ መሞት ለራስም ሆነ ለህዝብ ታላቅ ክብር ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ኦፒዲኦን ከህወሃት ጉዲፈቻ ልጅነት ወደ እውነተኛው የህዝብ ልጅነት የመመለሱ ውስጣዊ ትግል ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

መዘንጋት የሌለበት ነገር አለ። በወያኔ መንግስት ውስጥ ማንኛውም የራሱን ክብር ሸጦ የበላይ አለቆቹን ከወገቡ ጎብጦ ሲያገለግል የኖረም ሆነ በተቻለው አቅም በጊዜያዊ ጥቅም ሳይታወር ለህዝቡ ያለውን ወገንተኝነት ሲያሳይ የኖረ ካድሬ ዘላለም በወያኔ ስልጣን ወንበር ላይ መቀጠል አይፈቀድለትም። የሁለቱ ካድሬዎች ልዩነት ግን ለጠላት አጎብድዶ ራሱን ከመሸጥ እየተቆጠበ ለህዝብ ያለውን ወገንተኝነት ያስቀደመው ካድሬ ከስልጣን ቢነሳ ቢያንስ መውደቂያ ቦታና ለልጆቹ የሚያወርሰው የተሻለ ስም ያለው ሲሆን ከልቡ ለጠላት ታምኖ ሲያጎበድድ ኖሮ ከስልጣን የሚወረወረው ካድሬ ግን የመጀመሪያውን ካድሬ አይነት እድል የማያገኝ መሆኑ ነው።

እስከ ዛሬ ሲነሱና ሲወድቁ የኖሩትን የኦፒዲኦ ካድሬዎች ታሪክ ስንገመግም ይህ እውነት ይበልጥ ጎልቶ ይስተዋላል። ባንድ ወቅት "የኦሮምያ ፕሬዝዳንት" እየተባሉ ስማቸው ተቆልሎ ይታይ የነበረ የኦፒዲኦ ሹማምንት ዛሬ የት ደረሱ? "የመጀመሪያው የኦሮምያ (ኦፒዲኦ) ፕሬዝዳንት" የሆነው ሃሰን አሊ ዛሬ ምን ዋጠው? በፕሬዝዳንትነት ደረጃ "ሃገርን

ሲያስተዳደር” ነበር የሚባለው ሰው በሽምግልና ዘመኑ ለስደት ህይወት የተዳረገው ለምንድነው? ኣብሮው ሲሰራ ከነበረው መንግስት ጋር ብቻ ሳይሆን ከኣብራኩ ከወጣው ህብረተሰብ ተነጥሎ በስደት ኣገርም ከማህበረሰብ ተገልሎ ለብቸኝነት ህይወት የተዳረገበት ምክንያት ምንድነው?

ጁኔይዲ ሳዶስ የት ደረሰ? ትላንት ኣንጋፋውን የመጫና ቱለማ መረዳጃ ማህበር ባስዘጋበት ወቅት “ይህ ማህበር ስለ ኦሮሞ ለመናገር ምን ሞራል ኣለው?” በማለት ራሱን ያስገመተው ሰው ዛሬ ለምን የማህበሩ እጣ ገጠመው? ትላንት ከኣንድ ዩኒቨርሲቲ ብቻ ከ300 በላይ የኦሮሞ ተማሪዎች በብሄራቸው ማንነት ብቻ ተወንጅለው ሲባረሩ “መባረራቸው ትክክል ነው፣ ወደ ፊትም ይባረራሉ” ብሎ ጌቶቹን በደስታ ያስፈነጠዘው ግለሰብ ዛሬ ለምን ከነዚያ ተባራሪ ተማሪዎች ጋር በ UNHCR በራፍ ላይ በስደተኝነት ተሰልፎ ተገኘ? ትላንትና የኦሮሞ ተማሪዎች ኣናት ኣናታቸው ላይ በኣጋዚ ጦር ጥይት እየተመቱ በጭካኔ ሲገደሉ “እንኩዋን ተመቱ፣ ነገም ኣናት ኣናታቸው ላይ በጥይት እየመታን እንገድላቸዋለን” በማለት ታማኝነቱን ለጌቶቹ ያስመሰከረው የወቅቱ “ፕሬዝዳንት” ዛሬ በስርኣቱ ቀጭን ትእዛዝ በሃሰት ተወንጅላ የታሰረችውን ውድ ባለቤቱን ለምን ከእስር ማስፈታት ኣቃተው?

በደማቸው ኦሮሞ ሆነው በተግባራቸው ኦሮሞነታቸውን ከድተው ለጠላት በመላላክ ያሳለፉ እነዚህና ሌሎችም የኦፒዲኦ ካድሬዎች ዛሬ በጌቶቻቸው ትእዛዝ ከወንበራቸው ተነስተው ሲወረወሩ መውደቂያ ኣጥተው ይገኛሉ። ወደ ህብረተሰባቸው እንዳይመለሱ ህብረተሰቡ ኣይንህን ላፈር ብሎኣቸዋል። በታማኝነት ሲያገለግሉት ወደ ኖሩት ጠላት እንዳይመለሱ ጠላት በተገቢው ጊዜ እንደልቡ ከተጠቀመባቸው በሁዋላ የኣገልግሎት ዘመናቸው ሲያበቃ እንዳረጀ በቅሎ ሜዳ ላይ ጥሎኣቸዋል። ባጭሩ ከባህር የወጣ ኣሳ ኣይነት እጣ ገጠማቸው። ለወያኔ መንግስት ያበረከቱት ያልተቆጠበ ኣገልግሎት ከዚህ ውርደት ሊያድናቸው ኣልቻለም። ብዙ ሰዎች የኦፒዲኦ ካድሬዎችን ሲመክሩ “ወያኔ ከስልጣን ሲወገድ ከርሱ ጋር መቀሌ ኣትገቡምና እባካችሁ በጊዜ ከህዝባችሁ ጋር ታረቁ” የሚል ነበር። ዛሬ ግን ዘመን ተቀይሯል። የወገንን ምክር ችላ ያሉ የኦፒዲኦ ካድሬዎች ወርደታቸውን ለማየት ወያኔ እስኪወድቅ ድረስ እየጠበቁ ኣይደለም። ስርኣቱ በስልጣን እያለም የስራቸውን ዋጋ ሲያገኙ እነሆ ጊዜ እያሳየን ነው። በርግጥ ሃቅ ምን ያህል ተኣምር ሊሰራ እንደሚችል የሚመሰክር ክስተት እያየን ነው።

ህሊና ያለው ሰው ከዚህ ብዙ ሊማር ይችላል። ኦሮሞ ሆኖ ኦሮሞን ከድቶ ለወያኔ መላላክ መጨረሻው ውርደት መሆኑን ከተጠቀሱት ጥቂት ምሳሌዎች መረዳት ኣይከብድም። ዛሬ የስልጣን ወንበር ሞቆት ዘራፍ የሚለው የኦፒዲኦ ካድሬ ሁሉ በጊዜ ከጊዜ ተምሮ ከህዝቡ ጋር መታረቅ ኣለበት። ነግ በኔ ብሎ ማሰብ ካልጀመረ የነጁኔይዲ ኣይነት ክፉ እጣ እንደሚገጥመው መረዳት ኣለበት። እዚህ ላይ ኦሮሞን መክዳትና ከኦሮሞ መታረቅ የሚሉ ጽንሰ ሃሳቦችን በጥቂቱ ማብራራት ኣስፈላጊ ሳይሆን ኣይቀርም። ኦሮሞን መክዳት ማለት የኦሮሞ ህዝብ የሚመካበትን የራሱ የሆነ ድርጅት ከማጠናከር ይልቅ ጠላት ኦሮሞን ሊገዛበት ብሎ የጠፈጠፈውን ድርጅት ለጠላት ፋይዳ በሚውል መልኩ ለማደራጀት መድከም ነው። ከኦሮሞ መታረቅ ማለት ደግሞ ወያኔ ኦሮሞን ሊገዛበት የጠፈጠፈውን ድርጅት ከእጁ ፈልቅቆ በማውጣት መቆጣጠርና ለኦሮሞ ህዝብ መብት በቁርጠኝነት እንዲታገል ማድረግ፣ በዚህም ለኣንጋፋ የነጻነት ሃይል የማይናወጥ ኣጋር እንዲሆን ማስቻል ነው። ኦፒዲኦ ኣውነተኛ መረጋጋትና የህዝባዊ ድርጅትነት ክብር መጎናጸፍ የሚችለውም ያኔ ብቻ ነው።

የኦነግ ኢንፎ ዴስክ